# በበዓለ ሃምሳ ያሉት ረቡዕና ዓርብ ለምን ይበላሉ?

## በመጀመሪያ የምንጾምበትን ምክንያት እንገልጻለን

ለማናቸውም ተግባር ሁሉ መመሪያ
አለው መመሪያ የሌለው ሥራ ግቡን
አይመታምና ፣ እንደዚሁም ሁሉ ቤተ
ክርስቲያናችን ሰውና እግዚአብሔር
የሚገናኙበትን መመሪያ አውጥታ ዕለ
ትና ሰዓት ወስና ትመክራለች ታስተ
ምራለች።

ከብዙዎችም መገናኛዎች አንዱ
ጾም ነው ይህም ጾም በአምላክ ፈቃድ
ለሰው ልጆች የታዘዘና የተሰጠ ነው
መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም
ለኛ ያደረገልንን ቸርነት በሥራ ገልጦ
ሲአስተምረን የመጀመሪያው ተግባር
ጾምና ጸሎት ነው።

አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ጾመ፤ጸለየ
ሌሎችንም አስተማረ ማቴ- ም-፬ ቁ፥
፱ ቁ፥ ፲፰ ለሁሉም መመሪያ አለው
እንዳልነው ሁሉ ለዚህ ለተቀደሰ አላማ
አባቶች አንድ አንቀጽ ሰተውታል ከሰ
ባትም ከፍለውታል ከሰባቱም አንዱ
ዓርብና ረቡዕ ናቸው ።
የስድስቱን አጽዋማት ሁኔታና ዘርፎች
ከአስረዳን በኋላ «አዲ ረቡዓ ወአርበ
በኵሉ ሱባዔ ዘእንበለ መዋዕለ ፶ ወበ
ዓለ ጥምቀት ሶበ ኀብሩ ቦሙ»ይህም
ማለት ልደት፥ጥምቀት፤በዓለ ሃምሳ ካል
ዋሉባቸው በስተቀር በየሳምንቱ ዓር
ብና ረቡን መጾም ይገባል አርባ ጾም
ንና አርብና ረቡን የማይጾም ክርስቲ
ያን ካህን ቢሆን በክህነቱ ምዕመንም
ቢሆን በምዕመንነቱ ይመከር ይቀጣ
አልመለስም ቢል ይለይ የታወቀ ደዌ
ያለው ከሆነ ግን በደዌው ምክንያት
ነጻ ነው። ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፲፭
አርብና ረቡዕ የሚጾምበትም ምክንያት
ረቡዕ የምንጾምበት የዓለም መድኃኒት
ክርስቶስን መድኀኒትነቱን ያላመኑ
አይሁድ ለመግደል ፤ የጭካኔና የግፍ
ምክራቸውን ያጸኑበት ዕለት ስለሆነ
በጾም፥ በጸሎት፥ በስግደት እንድናስታ
ውሰው ቤተ ክርስቲያን በሕግ አድርጋ
ሠርታልናለች። ሁለተኛም ዓርብ ለዓ
ለም የተገረነው ተስፋ ሲፈጸም እርቃ
ኑን አድርገው በመስቀልላይ እጁን ዘር
ግቶ ደሙን ሲያፈስ ሥነ ፍጥረቶች ሌላ
መልክ አሳይተዋል በተለይም በሰማይ
፫ በምድር አራት በድምሩ ሰባት ተአ
ምራት ተፈጽመዋል ፀሐይና ጨረቃ
ብርሃናቸውን ነሥተው ዳመና-ጨለማ
ሁነዋል ከዋክብትም ረግፈዋል በምድ
ርም የቤተ መቅደስ መጋረጃ ከሁለት
ተሰንጥቋል መቃብራት ተከፍተዋል
ነፍሳት ተነሥተዋል አዕባን ተፈትተ
ዋል ይህ ሁናቴ የሚአመለክተን የመ
ከራና የኃዘን ዕለት መሆኑን ነው ስለ
ዚህ በየሳምንቱ እኒህን ሁለቱን ዕለታት
የምንጾምበት ምክንያት በዚህ ነው
በየሳምንቱ ሁለት ቀን ጾም እንዳለ
ሉቃስ በምዕራፍ አስራ ስምንት በቁ
ጥር ፲፪ በየሳምንቱ ሁለት ጊዜ እጦማ
ለሁ ከማገኘውም ሁሉ አሥራት አወ
ጣለሁ ሲል የተናገረውን ገልጦል
ናል ።
ታሪኩ እንዳይበዛ በማለት ነው እንጂ
በብሉይ ኪዳን የነበሩ አበውም ከሳም
ንትሁለት ቀን ይጾሙ እንደነበር ታሪክ
ያስተምረናል መጽሐፍ ቅዱስም ይነ
ግረናል ዓርብና ረቡዕን በሌላው ቀን
የምንጾማቸው ምክንያት ከዚህ በላይ
የተገለጸው ነው።

በበዓለ ሃምሳ ውስጥ ያሉትን የማን
ጾምበትን ምክንያት ግን ከዚህ ቀጥለን
እንገልጣለን። መድኃኒታችን ኢየሱስ
ክርስቶስ ከተጠመቀበት እስከሞተበት
ያሉትን፤ዘመናት ሁሉ በመራብ ፤ በመ
ጠማት፤በመወንጀል፡በመታሠር፡በመገ
ረፍ በመሰቀል በመሞት ከአሳለፈ በኋ
ላ በሱም ሞት ሲአዝኑና ሲጨነቁ ለነበ
ሩት ደቀ መዛሙርት ሞትን በሞት
ሽሮ ማለት የሰይጣንን መንግሥት ደም
ስሶ ተሰብስበው ሲጨነቁ ለነበሩት
በመካከላቸው ተገኝቶ ሰላም ለናንተ
ይሁን አላቸው ዮሐ- ፳ ቁ-፲፱ ሉቃ-፳፬
ቁ- ፴፮ ይህ ሰላምና ደስታ የተገኘበት
የዲያብሎስ መንግሥት የተደመሰሰ
በት ዘመን ስለሆነ አምሳውን ዕለታት
ሁሉ ክርስቶስ እንደተነሣባት ዕለት
ተቆጥረው የደስታ የዕረፍት ዕለታት
ይሆኑ ዘንድ ቤተ ክርስቲያናችን ወስ
ናለች ልደት፤ጥምቀት በዓለ ሃምሳ ከሚ
ውሉባቸው በስተቀር ያለው ስለዚህ
ነው ። ይህውም አምሳውን ቀን ሁሉ
ከእሑድ ለየት ያለ መልክ የምንሰጠው
በሥራ ነው ማለት እኒህ ሁሉ እለታት
ከሥራ ከተከለከሉ በሕዝብ ላይ ጉዳት
ስለሚደርስ ሥራውን እየሠሩ ፈጣሪአ
ቸውን በነግህ፤በቅዳሴ፥ በማኅሌት በመ
ዝሙር ከአመሰገኑ በኋላ አርብ ነው
ረቡዕ ነው ሳይሉ ሕዝበ ክርስቲያን
ሁሉ ከጾም ከስግደት ከቀኖና ተከልክ
ለው የሚወዱትን መብል መጠጥ ሳይ
ከለከሉ ደስታቸውን ይፈጽማሉ ምክ
ንያቱም በጾም፡በጸሎት ፤ በስግደት በቁ
መት፤በሀዘን ሲቀጠቀጡ የቆዩ ስለሆነ
የመከራ አጸፋው ደስታ ነውና የልደ
ትና የጥምቀትን አርብ ረቡዕ በገሃድ
ለውጥ ነው የበዓለ ሃምሳውን በምን
መልክ ነው የሚል ጥያቄ ቢኖር መልሱ
ይህ ነው በመጀመሪያው ሱባዔ እስከ
፲፪ ሰዓት በሁለተኛው ሱባዔ ማለት
ከቅድስት እስከ ኒቆዲሞስ ፲፩ ሰዓት
ሕማማትን ከሌሊቱ አንድ ሰዓት ጨ
ምሮ ፲፫ ሰዓት ይጾማል በሌላው ጊዜ
ያት ያሉት አጽዋማት ግን የሚጾሙት
፱ ሰዓት ነው ከዚህ ላይ ግን ከዘጠኝ
አብልጠን የጾምናቸው በሃምሳው ው
ስጥ ላሉት ዓርብና ረቡዕ ገሃድ ወይም
ተውላጥ ናቸው ከዚህም ሌላ ክርስቶስ
በመስቀል ላይና በመቃብር የቆየበትን
ብለን እንመልስለታለን ቅዳሜ ሥዑር
የተባለችውን ዕለት ጭምር በመጾም
በአክፍሎት የተገኘው የክርስቶስ ዕለተ
ትንሣኤ ሃምሳው ቀን እንዳንድ ዕለት
ሊቆጠር ቻለ ። ስለዚህም ባጠቃላይ
አምሳው ዕለታት ሊታዘንባቸው ሊጾ
ምባቸው የማይገቡ ለደስታ ብቻ የተ
መደቡ ስለሆኑ አንጾማቸውም ።

መምህር መርሐ ጽድቅ ገብረ
ሕይወት

www.ethiopianorthodox.org